ETHIOPIAN

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት
ETHIOPIAN SHIPPING & LOGISTICS SERVICES ENTERPRISE

ቀን/Date ጥር 16/2009 ዓ.ም

ቁጥር/Our Ref ቀኖኦ/ትጭክ/ግታ/025/2009

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋጋና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፣ ከጅቡቲ ወደብ እስከ መዳረሻ ደረቅ ወደብ ድረስ ያለውን የማጓጓዣ ወቅታዊ ዋጋ ስለማሳወቅ፣

ጽ/ቤታችሁ በቀረጥና ታክስ ማስፈፀሚያ ዋጋ ላይ የሚጨመሩትን ክፍያዎች ለቀረጥና ታክስ ማስፈፀሚያ ዋጋ ለማስላት ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ መዳረሻ ደረቅ ወደብና ቦንድድ ዌር ሀውስ መጋዘኖች ድረስ ያለውን ወቅታዊ የማጓጓዥያ ዋጋ እንድናሳውቃችሁ በ05/5/2009 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ድርጅታችንን ጠይቃችኋል ::

ስለዚህ ከየካቲት 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከትራንስፖርት ማህበራቶች ጋር ለ1 /አንድ/ ዓመት የሚሠራ በማጓጓዥያ ውል ስምምነት ሰነድ መሠረት እስከአሁንም ድረስ እየተሠራበት ያለውን የማጓጓዥያ ዋጋ እንደየተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም እንደየመዳረሻ ቦታቸው በሚከተለው ሠንጠረዥ አዘጋጅተን ልከናል::

ከሠላምታ ጋር

ለዋና ኦዲተር ጽ/ቤት
~~ለዋና ኦዲተር ጽ/ቤት~~
ዋና ሥራ አስፈጻሚ
ለ/ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ፣

- ለመልቲ ሞዳል ኦፕሬሽን መምሪያ
  ኢ.ኤ.ስ.አ.ድ

ለ/ቢሮ ኃላፊ
ለፍ/ቤ ኃላፊ
ለዋና ኦዲተር ጽ/ቤት

ሀ. የ2 ባለ 20 ወይም ባለ 40 ጫማ ኮንቴይነሮች የመጓጓዣ ዋጋ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ መጫን አቅም (የመንገድ ትራንስፖርት የመደበው የፖርታታ) | ከጅቡቲ--አዲስ አበባ (ኮሜት/ገላን) በኩንታል | ከጅቡቲ--ሞጆና አካባው ያሉ ቦንድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--ሰመራና አካባቢው ያሉ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--ድሬዳዋና አካባው ያሉ ቦንድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--መቀሌና አካባው ያሉ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--ኮምቦልቻና አካባው ያሉ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እስከ 250 ኩ/ል | 120 ብር | 114 ብር | 73 ብር | 105 ብር | 142 ብር | 113 ብር |
| 2 | እስከ 300 ኩ/ል | 111 ብር | 104 ብር | 68 ብር | 101 ብር | 133 ብር | 106 ብር |
| 3 | እስከ 350 ኩ/ል | 105 ብር | 98 ብር | 67 ብር | 99 ብር | 125 ብር | 99 ብር |
| 4 | እስከ 400 ኩ/ል | 100 ብር | 93 ብር | 63 ብር | 95 ብር | 116 ብር | 92 ብር |
| 5 | ባዶ ኮንቴይነር ወደ ጅቡቲ መመለሻ | 8000 ብር | 8000 ብር | 4000 ብር | 6000 ብር | 10000 ብር | 6000 ብር |

* Ethiopian Shipping & Logistics Services Enterprise * 2.34 Ministry of Transport

ለ. የ2 ባለ 20 ወይም 1 ባለ 40 ጫማ ኮንቴይነሮች የመጓጓዣ ዋጋ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ መጫን አቅም (የመንገድ ትራንስፖርት የመደበው የፖርታታ ) | ከጅቡቲ--አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--አዲስአበባ ውጭ እስከ 30ኪ.ሜ ርቀው የሚገኙ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--አዳማ ውስጥ የሚገኙ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ--ቢሾፍቱ ውስጥ የሚገኙ ቦንድ መጋዘኖች በኩንታል | ከጅቡቲ---ዱከም ውስጥ የሚገኙ ቦንድድ መጋዘኖች በኩንታል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እስከ 250 ኩ/ል | 136 ብር | 136 ብር | 109 ብር | 115 ብር | 117 ብር |
| 2 | እስከ 300 ኩ/ል | 125 ብር | 125 ብር | 103 ብር | 104 ብር | 108 ብር |
| 3 | እስከ 350 ኩ/ል | 115 ብር | 115 ብር | 98 ብር | 98 ብር | 105 ብር |
| 4 | እስከ 400 ኩ/ል | 108 ብር | 108 ብር | 93 ብር | 93 ብር | 100 ብር |
| 5 | ባዶ ኮንቴይነር ወደ ጅቡቲ መመለሻ | 8000 ብር | 8000 ብር | 8000 ብር | 8000 ብር | 8000 ብር |

* Ethiopian Shipping & Logistics Services Enterprise * Ministry of Transport 2.34

ሠንጠረዥ-1 ከጎረቤት ሀገራት ወደብ እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ እና ከወደብ እስከ መዳረሻ የጉ/ቀል/ጌቶች ወይም ደረቅ ወደቦች ያለው ርቀት በኪሎ ሜትር፤

| የትራንስፖርት መስመር ከመነሻ ወደብ | ከወደቡ እስከ ድንበር ያለው ርቀት | መዳረሻ ከተማ | ከወደብ እስከ መዳረሻ ከተማ ያለው ርቀት | ከወደብ እስከ ድንበር ያለው ርቀት ድርሻ በ% |
|---|---|---|---|---|
| ከጅቡቲ በጋላፊ መስመር | 217 | ጋላፊ | 217 | 100 |
| | | ሰመራ | 378 | 57.41 |
| | | አዳማ | 811 | 26.76 |
| | | ሞጆ | 836 | 25.96 |
| | | አዲስ አበባ | 909 | 23.87 |
| ከጅቡቲ በደወሌ መስመር | 116 | ደወሌ | 116 | 100 |
| | | ድሬዳዋ | 412 | 28.16 |
| | | አዳማ | 829 | 13.99 |
| | | ሞጆ | 854 | 13.58 |
| | | አዲስ አበባ | 927 | 12.51 |
| ኬንያ ሞምባሳ በሞያሌ መስመር | 1294 | ሞያሌ | 1294 | 100 |
| | | ሞጆ | 1994 | 64.89 |
| | | አዲስ አበባ | 2067 | 62.60 |
| ከበርበራ ሶማሊ-ላንድ በጅጅጋ መስመር | 241 | ቶጎ-ውጫሌ | 241 | 100 |
| | | ሞጆ | 864 | 27.89 |
| | | አዲስ አበባ | 937 | 25.72 |
| ፖርት ሱዳን በመተማ መስመር | 952 | መተማ | 952 | 100 |
| | | ባህር ዳር | 1333 | 71.42 |
| | | አዲስ አበባ | 1900 | 50.105 |